# የኤርትራ መንግስት የሳለው ካርታ

**ኢብሳ ነመራ** 09-05-17

*የኤርትራ መንግስት በኢትዮጵያ የእርስ በርስ ግጭት ሊቀሰቅስ ይችላል* ብሎ የገመተውን ማንኛውንም ጉዳይ ወደኢትዮጵያ ህዝብ ሲወረውር ቆይቷል። የእርስ በርስ ግጭት በመቀስቀስ ሃገሪቱን የማተራመስ ህልሙ ዛሬ፣ ዘንድሮ . . . በወረወረው አጀንዳ ባይሳካ ነገ፣ ከረሞ ሌላ የግጭት አጀንዳ ከመፈለግ እንደማይቦዝን የእስከዛሬ ባህሪው በግልጽ አሳየቶናል። በአንድ ሰው ፈላጭ ቆራጭነት የሚመራው የኤርትራ መንግስት እስካለ ደረስ ይህ ይቀጥላል። እስሩ የተሸሸጉት የትምክህትና የጠባብነት ህልማቸው ካልተሳካ ኢትዮጵያ እንድትፈርስ የሚፈልጉ ግለሰቦችና ቡድኖችም የዓለማችንን ብቸኛዋ ህገመንግስት አልቦና ከሩብ ክፍለዘመን በላይ ለሆነ ጊዜ አንድም ምርጫ ተካሂዶባት የማታውቀው የኤርትራ ፈላጭ ቆራጭ መሪ ኢሳያስ አፈወርቂ ኢትዮጵያን ያተራምሳል ብሎ ያመነበትን አጀንዳ ሲሰጧቸው ተቀብለው ወደሃገር ቤት ለማስረግ ከመፍጨርጨር እንዳይቦዝኑም ግልጽ ነው። ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ኢትዮጵያን የማተራመስ ተልዕኳቸውን ለማስፈጸም የሚጠቀሙት ማህበራዊ ሚዲያዎችን ነው።

በቁጥር ከአስር በላይ የሚሆኑት በአንድ ሰው ፈላጭ ቆራጭነት የሚመራው የኤርትራ መንግስት የከፈታቸው የማህበራዊ ሚዲያዎች *ኢትዮጵያን ያተራምሳል* በሚል ስሌት ተዘጋጅቶ የሚሰጣቸውን ማንኛውንም አጀንዳ ሳይሰለቹ በተደጋጋሚ፤ ምናልባትም በየሰአቱ የተለያየ አደናጋሪ ገጽታ እየሰጡ ያሰራጫሉ። የኤርትራ መንግስት ኢትዮጵያን የማተራመስ ጥረት ባለፉት ሁለት አስርት ዓመታት ሲካሄድ የቆየ ቢሆንም፣ በተለይ በኢትዮጵያ የማህበራዊ ሚዲያ ተጠቃሚዎች ቁጥር እጅግ በጨመረባቸው ያለፉት ሁለት ሶስት ዓመታት እጅግ ተጋግሏል።

ሰሞኑን የኤርትራ መንግስት ማህበራዊ ሚዲያዎች አንድ የግጭት አጀንዳ ሙጭጭ ብለው ይዘዋል። ይህም አንድ የኢትዮጵያን ክልላዊ መንግስታት አወቃቀር የሚያመለክት ካርታ ነው። ይህ ካርታ የትግራይ ክልል፣ በምዕራብ የሃገሪቱ አቅጣጫ የሱዳንን ድንበር ይዞ የምዕራብ አማራን፣ የቤኒሻንጉል ጉምዝን፣ የምዕራብ ኦሮሚያንና የጋምቤላን ክልሎች አካቶ እስከደቡብ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል ድረስ ይዘልቃል። ከደቡብ ህዝቦች አንድም መሬት አልነካም። የትግራይ ክልል የተባለው የደቡብ ብ.ብ.ህ ክልል በስተሰሜን ምእራብ ጫፍ የሚዛን ተፈሪ፣ በበቃ ለም መሬቶችን ሳይነካ ቆሟል። ከላይ ያሉትን መሬቶች በሙሉ ጨረጋግዶ እዚያ ጋር ለምን እንደቆመ ካርታውን የሰሩት ሰዎች ብቻ ናቸው የሚያውቁት፤

ይህ ካርታ በኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን የቴሌቪዥን ዜና ሽፋን ሆኖ ቀርቧል የሚል ወሬ ሰምቻለሁ። ካርታውን ሽፋን አድርጎ የቀረበውን ዜና ሰምቼዋለሁ፤ *ኢትዮጵያ በትግራይ ክልል በተከናወነው የተፈጥሮ ሃብት ጥበቃ ስራ ለዓለም አቀፍ ሽልማት ታጨች* የሚል ዜና ነው። የቀረበውን ካርታ ግን ልብ ብዬ አልተመለከትኩትም። እርግጥ ብመለከተውም ብዙ ዋጋ አልሰጠውም። የኢትዮጵያ ቴሌቪዥንን የሚያክል የሃገሪቱ አንጋፋ የቴሌቪዥን ጣቢያ በህገመንግስት ከተረጋገጠው የኢፌዴሪ ክልላዊ መንግስታት ካርታ የተለየ ካርታ ለተመልካች ማቅረቡ ግን ያስቆጣል። የዚህ አይነቱን ዝርክርክ አሰራር እንደቀላል ስህተት መቀበል ትንሽ ይከብዳል። ቴሌቪዥን ጣቢያው በስህተት ለቀረበው የኢትዮጵያ ካርታ ይቅርታ መጠየቁን ሰምቻለሁ፤ ይቅርታው መቼ በምን አይነት አኳኋን እንደቀረበ ግን አላውቅም፤ እኔ አልሰማሁትም። ያም ሆነ ይህ፤ *ኢቢሲ በቴሌቪዥን ስርጭቱ ሀሰተኛውን የኢትዮጵያ ካርታ አቅርቧል፤ ለዚህም ይቅርታ ጠይቋል* ብለን እንውሰድ።

አንድ መገናኛ ብዙሃን ባስተላለፈው መረጃ ላይ ስህተት ሲገኝ ለስህተቱ በይፋ ይቅርታ መጠየቁ ተገቢ ነው። እናም የኢቢሲ ቴሌቪዥን ይቅርታ ሊደረግለት ይገባ ይሆናል። ቴሌቪዥን ጣቢያው ከዚህ ቀደምም ተመሳሳይ ስህተት ፈጽሞ የነበረ በመሆኑ

አሁንም ላለመድገሙ ግን ዋስትና የለንም። ምናልባት ቴሌቪዥን ጣቢያው የኤርትራ መንግስት የትርምስ ስትራቴጂ አስፈፃሚ ሰርጎ ገብ ዘልቆት እንዳይሆን ያሰጋናል። ከኢቢሲ የቦርድና የማኔጅመንት አባላት ጀምሮ፣ በየደረጃው ያሉ አዘጋጆች ለኤርትራ የትርምስ ስትራቴጂ አጀንዳ አስፈፃሚ ላለመሆን መጠንቀቅ ይኖርባቸዋል። ይህን ጥፋት እየደገሙ፣ ሁሌም በይቅርታ እየታለፉ መዝለቅ የሚችሉ አይመስለኝም። የፈጸሙት ስህተት ሊያስከትል በሚችለው ስጋት ልክ ሊጠየቁ ይገባል። በሃሰተኛ መረጃ ህዝብን ከህዝብ ማጋጨት የተከለከለው ለግል መገናኛ ብዙሃን ብቻ አይደለምና፤

ይህ የትግራይን ክልል በምእራብ አቅጣጫ በቀጭኑ እስከ ደቡብ ክልል ስቦ የለጠጠ ካርታ በህገመንግስት ተቀባይነት ያገኘውን የኢፌዴሪ የክልሎች የወሰን አከላለል አይወክልም። የትግራይ ክልላዊ መንግስትም ይህን ካርታ *ካርታዬ* ብሎ አያውቅም። ተጠቅሞበትም አያውቅም። ይህን ካርታ የሰራ አካል *የኢትዮጵያን ህዝብ እርስ በርስ ለማተራመስ ያስችላል* ያለውን ማንኛውንም ጉዳይ፣ ብስል ከጥሬ ሳይለይ እየለቃቀመ የሚያሰራጭ አካል ከመሆን የተለየ ሊሆን አይችልም። ይህ ካልሆነ ደግሞ እብድ ነው።

ይህ ካርታ በድረ ገጾች ላይ ተለጥፎ ሊሆን ይችላል። በድረ ገጾች ላይ መለጠፉ፣ የለጠፉትን አካላት ማንነት አይለውጠውም። ድረ ገጽ ላይ መለጠፉ ብቻም ተቀባይነት እንዲኖረው አያደርገውም። ማህበራዊ ሚዲያ ድረ ገጾችን ጨምሮ ማንም የፈለገውን የሚያወራበትና እስካሁን ባለው አሰራር ከተጠያቂነት ስርአት ያፈነገጠ ሚዲያ ነው። ማንም የፈለገውን ጉዳይ ለፈለገው ዓላማ ማህበራዊ ሚዲያዎች ላይ ሊለጥፍ ይችላል። በማህበራዊ ሚዲያዎች ላይ የሚቀርበውን ዝባዝንኬ አጣርቶ ትክክለኛውን መወሰድ የተጠቃሚው አካል ሃላፊነት ነው። ማህበራዊ ሚዲያ ላይ የተለጠፈን በሙሉ የሚያጋብስ ግለሰብ እንደማህበራዊ ሚዲያው የተዘባረቀ ከመሆን አያመልጥም።

ሰሞኑን የኤርትራ መንግስት ማህበራዊ ሚዲያዎች *የትግራይ ክልል መሬታችሁን ሊወስድ ነው* ብለው ያስተላለፉትና እያስተላለፉት የሚገኙት ካርታ በእርግጠኝነት በኤርትራ መንግስት እና/ወይም በባለሚሎቹ የተሰራ ነው። ዓላማውም የትግራይን ህዝብ ከተቀሩት የኢትዮጵያ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች ጋር ማጋጨት ነው። የተቀሩት ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች አባላት በትግራይ ህዝብ ላይ እንዲነሱ የመቀሰቀስ እኩይ ዓላማ ያዘለ ነው።

ኢትዮጵያ ፌደራላዊ ስርአት የምትከተል ሃገር ነች። የፌደራል መንግስቱ በብሄራዊ ማንነትና በህዝብ አሰፋፈር ላይ ተመስርቶ የተዋቀሩ ራሳቸውን በራሳቸው የሚያስተዳድሩ ዘጠኝ ክልሎች አሉት። እነዚህ በኢፌዴሪ ህገመንግስቱ ላይ የሰፈሩት ክልሎች - የትግራይ፤ አፋር፤ አማራ፤ አሮሚያ፤ ሶማሌ (በኋላ በክልሉ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ሶማሌ ተብሏል)፤ ቤኒሻንጉል/ጉምዝ፤ የደቡብ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች፤ የጋምቤላ ህዝቦችና የሃራሪ ህዝብ ክልሎች ናቸው።

ክልሎቹ የተዋቀሩት፣ በመልከአምድር አይደለም፤ በዘፈቀደም አይደለም፤ በአንድ አካል ፍላጎትም አይደለም። ከዚህ ይልቅ በህገመንግስቱ አንቀጽ 46 ንኡስ አንቀጽ አንድ መሰረት ነው። ይህ አንቀጽ *ክልሎች የተዋቀሩት በህዝብ አሰፋፈር፣ ቋንቋ፣ ማንነትና ፍቃድ ላይ በመመስረት ነው* ይላል። እናም ማንም ተነስቶ የፌደራል መንግስቱም ጭምር የክልሎችን ወሰን ሊቀይር አይችልም። የፌደራሉ መንግስት ህገመንግስት (የኢፌዴሪ ህገመንግስት) የፌደራሉን ክልሎች ማንነት የሚገልጽ ቢሆንም፣ የየትኛው ክልል ወሰን የት ድረስ እንደሚዘልቅ፣ የትኛው በየትኛው አቅጣጫ ከማን ጋር እንደሚዋሰን የሚገልጸው ነገር የለም። ይህ የክልሎች ጉዳይ ነው። ድንበራቸውን የወሰኑት ክልሎች ናቸው። የፌደራል መንግስቱ በክለሎች ነው የተመሰረተው። የፌደራል መንግስቱ ስልጣን በሙሉ ከክልሎች የመነጨ ነው።

በህገመንግስቱ አንቀጽ 50 መሰረት የፌደራል መንግስትና ክልሎች የየራሳቸው የህግ አውጪነት፣ የህግ አስፈፃሚነትና የዳኝነት ስልጣን አላቸው። የክልል ከፍተኛ የስልጣን አካል የክልሉ ምክር ቤት ነው፤ ተጠሪነቱም ለሚወክለው ክልል ህዝብ ነው። የክልል

ምክር ቤት የክልሉ የህግ አውጪ አካል ነው። የኤፌዴሪን ህገመንግስት መሰረት በማድረግ የክልል ህገመንግስት ያዘጋጃል፣ ያጸድቃል፤ ያሻሽላል። የክልሎች ድንበርና አወሳኞች የሚገለጹት በክልል ህገመንግስት ላይ ነው። እናም የትግራይም፣ የአማራም፣ የቤኒሻንጉልም፣ የኦሮሚያም፣ የጋምቤላም፣ የደቡብ ብ.ብ.ህም ክልላዊ መንግስታት ህገመንግስት ወሰን የኤርትራ መንግስት ሰሞኑን ያሰራጨውን ካርታ የሚመለከት ወሰን የላቸውም።

የትግራይ ክልላዊ ህገመንግስት፣ ክልሉ በሰሜን ከኤርትራ፣ በምስራቅ ከአፋር፣ በደቡብና ደቡብ ምእራብ ከአማራ፣ በምእራብ ከሱዳን እንደሚዋሰን ነው የሚገልጸው። የአማራ ክልላዊ ህገመንግስት ደግሞ በስተሰሜን ከትግራይ፣ በምስራቅ ከአፋር፣ በደቡብ ከኦሮሚያ፣ በምእራብ ከቤኒሻንጉል ጉምዝና ሱዳን ጋር እንደሚዋሰን ነው የሚገልጸው። እውነታው ይህ ከሆነ የአማራ፣ የቤኒሻንጉል ጉምዝ፣ የኦሮሚያ፣ የጋምቤላ ክልሎች በስተምእራብ የሚዋሰኑት፣ የደቡብ ብ.ብ.ህ ክልል ደግሞ በሰሜን ምስራቅ ጫፉ የሚዋሰነው የትግራይ ወሰን ከየት የመጣ ነው? ይህ በካርታው ውስጥ የተካተቱ ክልሎች በህገመንግስታቸው ላይ ያላሰፈሩት ካርታ በኤርትራ መንግስት የተሳለ መሆኑን በእርግጠኝነት መናገር ይቻላል።

ይህ የትግራይ ህዝብና የክልሉ መንግስት የማያውቁት፣ በህገመንግስታቸውም ላይ ያላሰፈሩት፣ የፌደራል መንግስቱ አካል ሲሆኑም ያላሳወቁት ካርታ በኤርትራ መንግስት ተዘጋጅቶ የተሰራጨበት ዓላማ ግልጽ ነው። የትግራይን ህዝብ ነጥሎ ከሌሎች ጋር ማጋጨት፤ በቃ፤ የማጋጨት ሴራ መጠንሰሱና ግጭት ለመቀስቀስ መሞከሩ ግን በዚህ አያበቃም። በአማራና በኦሮሚያ፣ በደቡብና በኦሮሚያ፣ በኦሮሚያና በኢትዮጵያ ሶማሌ፣ በአፋርና በኦሮሚያ፣ በአፋርና የኢትዮ ሶማሌ ወዘተ. መካከልም ይቀጥላል። እናም እዚሁ ላይ በቃህ ሊባል ይገባል።

የኤርትራ መንግስት ብቻውን ኢትዮጵያን የማተራመስ ዓላማውን የመስፈጸም አቅም የለውም። ይህን ለማድረግ መሞከርም አይችልም። የማተራመስ ሙከራውን የሚያደርገው በሰሩ ባደሩ ለኢትዮጵያ ህዝብ፣ ለአማራ፣ ለኦሮሞ … ህዝብ ተቆርቋሪ መስለው የሚቀርቡ የበግ ለምድ የለበሱ ቀበሮ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያን አማካኝነት ነው። የተጠቀሰውን የኤርትራ መንግስት *ኢትዮጵያን ለማተራመስ ይጠቅም ይሆናል* በሚል ስሌት የሳለውን ካርታ እየለጠፉ ግጭት ለመቀስቀስ የሚንፈራገጡት መረጃ ዶት ኮም፣ ዘሃበሻ፣ ኢትዮጵያን ዲጂ የተሰኙት ማህበራዊ ሚዲያዎች በቀጥታ በኤርትራ መንግስት ትእዛዝ የሚሰሩ ናቸው።

በሌላ በኩል የኤርትራ መንግስት የትርምስ ስትራቴጂ አስፈፃሚዎች ኢትዮጵያውያንን እርስ በርስ የማጋጨት ሴራ ሊሳካ የሚችለው ኢትዮጵያውያን በኤርትራ ማህበራዊ ሚዲያዎች የሚሰራጨውን የፈጠራ ወሬ እስከተቀበሉ ድረስ ብቻ ነው። የወሬው ዓላማ የእርስ በርስ ግጭት በመፍጠር ሃገሪቱን ዳግም ሃገር ልትሆን በማትችልበት ሁኔታ ማፍረስ መሆኑን ማወቅ የኢትዮጵያውያን ድርሻ ነው። የገዛ ቤቱን በእጁ የሚያፈርስ ሞኝ ላለመሆን መጠንቀቅ የኢትዮጵያውያን ድርሻ ነው። በተለይ በኢፌዴሪ ህገመንግስት ላይ፣ በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ስርአት ላይ እንዲሁም በክልሎች ስልጣንና አሰራር ላይ ግንዛቤ የሌላቸው ወጣቶች የውዥንብሩ ሰለባ እንዳይሆኑ ማንቃት ከሁሉም ነፍስ ያወቀ ዜጋ ይጠበቃል። በአጠቃላይ፤ ሰሞኑን በኤርትራ ማህበራዊ ሚያዎች እየተሰራጨ ያለው ካርታ በኤርትራ መንግስት የተዘጋጀ ኢትዮጵያውያንን የማተራመስ ዓላማ ያለው መሆኑ መታወቅ አለበት፤ ንቁ፤